# የአማራ ፋኖ ድምፅ
# The Voice of Fano

በወቅታዊ አርዕስት በአፋሕድ የፖለቲካ ጉዳዮች መምሪያ እየተዘጋጀ የሚቀርብ
Issued by AFPO Department of Political Affairs on Current Topics

Vol. 1; No. 4
አንደኛ ዓመት አራተኛ እትም

Wednesday, September 10, 2025
ረቡዕ ጳጉሜ ፭ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.


## ርዕሰ አንቀጽ

### የፖለቲካ ማኅበረሰብ እና የትጥቅ ትግል

**1. መግቢያ**

በዘመናዊ አጠራር ሀገር ለመባል አምስት መሰረታዊ ነገሮች (the five essential elements of state) መሟላት አለባቸው እነዚህም፡ ወሰኑ የታወቀ መሬት፣ **ሕዝብ**፣ መንግስት፣ ሉዓላዊነት እና ዓለም-ዓቀፍ እውቅና) ናቸው። ሌሎችን የሀገር ምሰሶዎች ለጊዜው እንተዋቸው እና ሕዝብ የሚለው ጉዳይ የዚህ ጽሁፍ አርዕስት ይሆናል። ሕዝብ ለአንድ ሀገር እንደየሁኔታው ፀጋ (Asset) ወይም እዳ (Liability) ሊሆን ይችላል። የአንድ ሀገር ሕዝብ በአግባቡ የሰለጠነ፣ የተደራጀ እና እጣ ፈንታውን በጋራ መወሰን የሚችል ከሆነ ይህ ሕዝብ ጸጋ ነው ልንለው እንችላለን። ይህም በብዙ የምዕራቡ ዓለም እና በእስያ ሀገራት ተስተውሏል። በተቃራኒው፣ አንድ ሕዝብ በብሄር፣ በሀይማኖት፣ በጎሳ እና በሌሎች ንዑስ ማንነቶች ተከፋፍሎ፣ የጋራ እጣ ፈንታውን ዘንግቶ፣ ዓለም ዐቀፍ ሁኔታውን ወደ ጎን ብሎ ቅርጽ አልባ ጉዞ ላይ ካለ ይህ ሕዝብ እዳ ነው፣ ለማልማትም ለመልማትም መነሻና መድረሻውን ለመለየት ስለሚያስቸግር እንደተተራመሰ ይቀጥላል። ይህ ሁኔታ በብዙ የአፍርካ ሀገሮች እና በተወሰኑ የእስያ ሀገሮች እንዲሁም በደቡብ አሜርካ ተፈጥሯል። አንድን ሀገር ሕዝብ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ እና የሕዝቡን ኑሮ ለማዘመን በመጀምሪያ ደረጃ ሕዝብን ማስተማር፣ ማንቃት፣ ማደራጀት እና ማታገል ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ተፈጥሯል ለማለት ያስችላል።

**2. የፖለቲካ ማኅበረሰብ ማለት ምን ማለት ነው**

የፖለቲካ ማሕበረሰብ (political community) በአንድ ሀገር ወይም ብሄር ውስጥ ያለ ሕዝብ የጋራ ጉዳዮችን በአንድነት ቅርጽ የሚሰጥበት፣ የጋራ ጉዳይ ላይ የተበታተነ እይታ እና አስተሳሰብ የማይፈጥር፣ እርስ በርስ የሚከባበር እና በጋራ የሚወስኑበት ሂደት ካለ የፖለቲካ ማህበረሰብ እንደተፈጠረ የተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ለምሳሌ ያህል የፖለቲካል ሳይንስ ጠበብቱ አርስቶትል የተበታተነ እና በጋራ እጣ ፈንታው ላይ ያልተደራጀ ሕዝብ ለምንም ነገር እንደማይጠቅም እና ወደየት መሄድ እንዳለበት አቅጣጫ ማስቀመጥ እንደማይችል በግልጽ አብራርቷል። የተደራጀ ማሕበረሰብ በፖለቲካዊ ህይወቱ ለአምባገነን ስርዓት እንዳይጋለጥ መከላከል የሚችል እና በስልጣኔም በዝባዥ እና ተበዝባዥ እንዳይኖር የተመጣጠነ ሕዝባዊ እድገት እንዲኖር ጉልህ አስተዋጾ እንደሚኖረው ያትታል። ይህ ማሕበረሰብ የፖለቲካ ማሕበረሰብ ለመባል የሚያስችለውን ደረጃ አሟልቷል ማለት ነው።

ቶማስ ሆብስ፣ Leviathan በሚለው መጽሀፉ ላይ የተደራጀ ሕዝብ ሊኖረው ስለሚችለው ሚና በሰፊው አብራርቷል። ሆብስ፣ የፖለቲካ ማሕበረሰብ አንድን ሀገር ከብጥብጥ እና ከዘፈቀዳዊ ኑሮ ሊያላቅቅ የሚችል እንዲሁም በፖለቲካ የነቃ ማሕበረሰብ ለሀገር ጠቃሚ ተቋም ለመመስረት ትልቅ ሚና እንዳለው፣ አምባገነናዊ ስርዓት እንዳይመጣ እና ሀገር ወደ ትርምስ እንዳትሄድ ብቸኛው መፍትሄ እንደሆነ ይዘርዝራል። ከላይ የተዘረዘሩት ሀሳቦች የሚያስረዱን አንድ ቁምነገር ቢኖር የተደራጀ እና የፖለቲካ ንቃተ-ህሊናው የዳበረ ሕዝብ የተረጋጋ እና ዘላቂ ሰላምን ሊያመጣ የሚችል ስርዓት መፍጠር እንደሚችል ነው።

**3. ጠንካራ የፖለቲካ ማኅበረሰብ የፈጠሩ ድርጅቶች እና ውጤቶቻቸው**

ጠንካራ ድርጅቶች ሀገራቸውን ወደተሻለ ደረጃ ለማሻገር የተለያዩ ሥራዎችን ይሰራሉ። ከነዚህ አንዱ እና ዋነኛው ሕዝብን በጋራ ለሀገሩ አንድነት እንዲሰለፍ ማስተማር እና ማደራጀት ነው። ይህ ሕዝብን በአንድነት እንዲሰለፍ የማድረግ ሥራ እጅግ አስቸጋሪ፣ በርካታ ዝግጅቶችን የሚጠይቅ፣ ርዕይ መንደፍ እና ሩቅ አሳቢ መሆንን ይጠይቃል። ይህን በአግባቡ በተግባር ያሳዩ ድርጅቶች ሀገራቸውን ትልቅ ቦታ አስቀምጠዋል። ከዚህ በታች የተጠቀሱት የቬትናም እና የቻይና የትግል ጉዞ ብዙ ሀገሮችን ያስተማረ እና አሻራቸው ዘላቂ ነው። የሀገሮቹ ነባራዊ የትግል ሁኔታ ለኛ ሀገር በቀጥታ ሊወሰድ ባይችልም፣ የፖለቲካ ማሕበረሰብ የፈጠሩበት መንገድ ግን በማንኛውም ሰዓት እና ጊዜ ልንማርበት ይገባል።

**3.1. የቬትናሙ ሆቺሚን እና ኮሚኒስት ፓርቲ**

በዓለማችን ውስጥ በ20ኛው ክፍለ-ዘመን ለነጻነታቸው መራራ ትግል ካካሄዱ ሀገሮች በግንባር ቀድምትነት የምትጠቀሰው ሀገር ቬትናም ናት። ቬትናም በቀዝቃዛው ጦርነት የነበረውን የዓለም ሀገራት በሁለት ጎራ መከፈል መሠረት አድርጎ ሰሜን እና ደቡብ ቬትናም ተብለው ሰሜኑ ሶሻሊስት ደቡቡ ደግሞ የካፒታሊስት አቀንቃኝ ሲሆን፣ ደቡቡ ክፍል በመጀመሪያ በፈረንሳይ መንግስት በኋላ ደግሞ በአሜሪካ መንግስት ድጋፍ እስከ ሽንፈት (ገጽ 2 ላይ ይቀጥላል።)





### መልካም አዲስ ዓመት፣ ፳፻፲፰፣ ከአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አፋሕድ)

በዚህ የአዲስ አመት ዋዜማ፤ የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም ችግሮችን ሁሉ ተቋቁሞ ለዘለቀው ለመላው የአማራ ሕዝብ እና ሕዝባቸውንና አገራቸውን በክብርና በመስዋዕትነት እየጠበቁ ላሉት ታጋይ ፋኖዎች ልባዊ የአዲስ ዓመት ምኞቱን ያቀርባል። አዲስ ዓመት የቀን መቁጠሪያ ለውጥ ብቻ አይደለም - የአንድነት፣ የሥርዓት እና የዓላማ ጥሪ ዘመን ነው። የአማራ ተጋድሎ ወሳኝ ወቅት ላይ በደረሰበት በዚህ ወቅት፤ አፋሕድ ሁሉን የፋኖ አደረጃጀቶች ባማከለና በማያሻማ መርኅ፣ በጠንካራ መዋቅር እና በማያወላውል ቁርጠኝነት ለሚመሠረት አንድነት ከምንጊዜውም በላይ ዝግጁ ነው።
(ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል።)

### A New Year's Message from Amhara Fano People's Organization (AFPO)

As we welcome 2018 E.C., the Amhara Fano People's Organization (AFPO) extends its heartfelt New Year greetings to all Ethiopians and, in particular, to the indomitable Amhara people and patriots who continue to defend their people and homeland with honor and sacrifice.
(Continues on Page 4)



## Editorial

### Political Community and Liberation Struggle!

**1. Introduction**

To qualify as a modern nation-state, five essential elements of statehood must be fulfilled: a defined and accepted territory, population, government, sovereignty, and international recognition. Among these, the issue of population will be the focus of this article, even if other aspects of a nation are in place for the time being. A nation's population can be an asset or a liability depending on its condition. If a nation's people are properly educated, organized, and capable of pursuing their interests collectively, we can consider this population an asset. This has been proven in many parts of the world and in Asian countries. Conversely, if a population is divided by ethnicity, religion, race, and other divisive identities, unable to pursue collective interests, and heading toward conflict that disregards global realities, this population becomes a liability, as it hinders both survival and development. This situation has arisen in many African countries, certain Asian nations, and Latin America. To elevate a nation's population to a better level and mobilize it, the initial step requires educating, mobilizing, organizing, and empowering the people. This can be said to give rise to a political community.

**2. What Does "Political Community" Mean?**

Experts in various fields agree that a political community exists when the population within a nation or country addresses common issues with unity, develops a shared perspective and mindset on collective matters, communicates with each other, and follows a common path. For example, Aristotle, the father of political science, clearly stated that a population that is uneducated and disorganized cannot achieve anything and cannot decide where to go. A well-organized community can prevent the emergence of anarchy in political life, ensure measured popular development without tyranny, oppression, or exploitation, and play a crucial role. This community has reached the level that qualifies it to be called a political community. (Continued on page 2)

### ከድሮን ጥቃት ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ መርሆች

ዘመኑ በከፍተኛ ደረጃ ቴክኖሎጅ የተራቀቀበት ወቅት ነው። በብዙ ሀገራት የሰው አልባ አውሮፕላን የጦርነትን ፋሽን ቀይሮታል። የትኛውንም ያክል ርቀት በረሃ ላይ ብንቀመጥ አንድ ማዕከል ኮምፒዩተር ጣቢያ ላይ ሆኖ ወይንም በእጃችን ስልክ በተጫነ አፕሊኬሽን በመጠቀም የተለያዩ ድሮኖችን ልኮ ጥቃት መፈፀም ይቻላል። ድሮኖች በጥቆማ በሚሰጣቸው መረጃ ካርታ በመጠቀም ወይንም በቀጥታ በአየር ላይ ሆነው በከፍተኛ ካሜራ በመታገዝ በሚሰሩት የአሰሳ ውጤት ወይንም በእጅ ላይ ያለ ስልክን ወይንም ሌላ ኤሌክትሮኒክስ ጂፒኤስን በመጠቀም በየትኛውም ሰዓት (ምሽትን ጨምሮ) ጥቃት መፈጸም ይችላሉ። ስለሆነም ዘመኑን የዋጀ የትግል ስልትና ስትራቴጂ በመንደፍ የጠላትን የትኛውንም የጥቃት ኢላማ ማክሸፍ በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል። (ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል።)

## የፖለቲካ ማሕብረሰብ እና የትጥቅ ትግል (ከገጽ 1 የቀጠለ)

ድረስ ቆሞ ቆይቷል። ይህን የቬትናም አንድነት አደጋ ውስጥ መውደቁን የተረዱ የሀገሪቱ ባለራዕይ ታጋዮች የቬትናም ሕዝብ ለነጻነቱ እና አንድነቱ ማታገል እንዳለባቸው ወስነው ተነሱ። ከነዚህ ውስጥ ዋናው ሆቺሚን ነው። ሆቺሚን ከ1924-1930 በቻይናና በቬትናም በመዘዋወር ለዚህ ውስብስብ ትግል ግንባር ቀደም አመራር ሊሰጥ የሚችለውን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ለማቋቋም ከፍተኛ ዝግጅት አደረገ። በመጀመሪያም የቬትናም አብዮታዊ ወጣቶች ማኅበር የተባለውን "ወጣት" በተባለው ጋዜጣ ወጣቱን ለትግል ቀሰቀሰ። በዚህ ዓይነት ከብዙ ጥረትና ትግል በኋላም በ1930 የኢንዶ ቻይና ኮሚኒስት ፓርቲን (በኋላ የቬተናም ነጻነት ፓርቲ፣ ዛሬ ደግሞ የቬተናም ኮሚኒስት ፓርቲ) መሠረተ።

እ.አ.አ. በ1935 ዓ.ም ሞስኮ ውስጥ የተካሄደው የኮሚኒስቶች ስብሰባ አንድ ሰፊ ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆነ ዴሞክራሲያዊ ግንባር እንዲቋቋም በወሰነው መሠረት ***ሆቺሚን ቬትሚን*** የተሰኘውን ሰፊ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ግንባር በማቋቋም መላውን ሕዝብ በትግሉ ለማሳተፍ ችሏል። ዲዮን ቢየን ፉ በተባለው ታሪካዊ ስፍራ የቬትናም አርበኞች የፈረንሳይን ጦር በማሸነፋቸው ፈረንሳይ በጄኔቩ ስምምነት መሠረት የቬተናምን አንድነት በመረዳት የሰላም ውል ፈረመች። ነገር ግን ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በፈረንሳይ እግር በመተካት የደቡቡን ክፍል ለመቁረስ የጦር ሰፈር በመሥራትና በውስጥ አርበኞች በመጠቀም ጦርነት ከፈተ። የቬተናም ሕዝብ በዓለም ተራማጅና ሰላም ወዳድ ኃይሎች እየታገዘ በቆራጥነት እብሪተኛውን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ተቋቋመ። የአሜሪካ ጦር ከግማሽ ሚሊዮን ወታደሮች በላይና በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ቢያፈስም የቬትናምን ሕዝብ ሊያንበረክክ አልቻለም። ሕዝቡም ይሄንን ድል ሊቀዳጅ የቻለው በቬትናም ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር ነው። የዚህ ፓርቲ ዝነኛ መሪ የነበረው ሆቺሚን የሕይወት ዘመኑን በሙሉ በትግል ያሳለፈና ታሪኩም ከቬትናም ሕዝብ የትግል ታሪክ ጋር በቅርብ የተሳሰረ ታላቅ መሪ ነበር። ሆቺሚን ለዚህ ድል የበቃው አንድ የፖለቲካ ማሕብረሰብ በጋራ እጣ ፈንታ አስተሳስሮ በማታገሉ ነው።

### 3.2. ማኦ ዜዶንግ እና የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ

በዓለማችን ላይ በከፍተኛ ረሀብ እና ችግር ይሰቃዩ ከነበሩ ሀገሮች አንዷ ቻይና ናት። ይህን የቻይና ችግር በአግባቡ የተረዳው ማኦ፣ የቻይና ሕዝብ በአብዛኛው በኋላ ቀር ግብርና እንደሚመራ፣ ሕዝቡን ለማታገል እና ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ ገበሬውን መሠረት ያደረገ የትግል ስልት መንድፍ እንዳለበት እና ከተሜውን መሠረት ያደረገ ትግል የትም እንደማያደርስ ደመደመ። ለዚህም ነው ጦርነቱ ሕዝባዊ ማዕበልን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት በማለት አቅጣጫ ያስቀመጠው። በእቅዱ መሠረት ገበሬው በትግል ውስጥ እንዲሳተፍ የተለያዩ አደረጃጀቶችን በገጠሩ ክፍል አቋቁሟል። ከነዚህ ውስጥ የገበሬዎች ማኅበር፣ የሰላም እና ጸጥታ ዘርፍ እና የቢሮክራሲ አስፈጻሚዎች እና ሌሎችንም መዋቅሮች እንዲቋቋሙ አድርጓል። ይህን ሲያደርግ የነበረው የገጠሩ ማኅበረሰብ በአብዮታዊ ትግሉ ውስጥ በባለቤትነት መሳተፍ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የፖለቲካ ንቃተ ህሊናቸው እያደገ እንዲመጣ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየወጡ ያሉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ድርጅቶች በትግል ወቅት በተቆጣጠሩት አካባቢ ሁሉን አቀፍ አስተዳደር የዘረጉ እና ዝምብለው ጦርነት ብቻ የሚያካሂዱ ንጽጽራዊ ጥናት ተካሂዶ ሁሉን አቀፍ አስተዳደር በትግል ወቅት የመሰረቱት ስልጣን ከያዙ በኋላ ውጤታማ አስተዳደር እና ሀገር እንደመሰረቱ እና ጦርነት ብቻ የሚያካሂዱት ደግሞ በሂደት እንደተዳከሙ፣ ወይም ለውጥ እንዳላመጡ ያረጋግጣል። የነ ማኦ የትግል ስልት ሁሉን አቀፍ አስተዳደር በመዘርጋት ለረጅም ዘመን ልምምድ ሲያደርጉ ስለነበር መጨረሻቸው በጣም ውጤታማ ሆኗል። ለዚህ ውጤት ያበቃቸውም በአመለካከቱ እና በተግባራዊ እንቅስቃሴው ተቀራራቢ የሆነ የፖለቲካ ማሕብረሰብ መፍጠር መቻላቸው ነው።

ማኦ ሕዝቡ በትግሉ ላይ ያለው አመለካከት የጠራ እንዲሆን ፕሮግራማቸውን በቀዩ መጽሀፍ (Red Book) ላይ በመቀመር በቀላሉ ለሕዝቡ እንዲደርስ በማድረግ ሕዝቡን አስተምረዋል። ሚሊዮን ቻይናውያን ትንሿን ቀይ መጽሐፍ ልክ እንደ ሃይማኖት ቀኖና ተቀበሏት። ቀዩ መጽሐፍ በዓለም ገበያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ በብዛት የተሸጠ ሲሆን እስካሁን ድረስ 900 ሚሊዮን ገዳማ ቅጅ ተሽጧል። ስለ ቻይናውያን አንድነት ስናወራ ቻይና ውስጥ የጎሳ፣ የሀይማኖት እና ሌሎች ማንነቶች ልዩነት ሳይኖር ቀርቶ አይደለም፣ ነገር ግን እንደነ ማኦ ያሉ ምርጥ የአንድነት ንድፍ ቀማሪ ስላላቸው ክፉውን ዘመን በመስዋዕትነትም ቢሆን ተሻግረውታል። የዛሬዋ የቻይና ልዕልና ስናይ በብዙ መስዋዕትነት የተገነባው የፖለቲካ ማሕብረሰብ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

### 4. የፖለቲካ ማሕብረሰብ በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በርካታ አስተዋጾ ያደረገች ሀገር ናት። ኢትዮጵያዊያን ከሀገራቸው አልፎ ለሌሎች ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ጉዞ ተምሳሌት የሚሆን አስተዋጾ ያደረጉ ናቸው። ነገር ግን ሀገራቸውን ከውጭ ጠላት በጋራ የተከላከሉትን ያክል በሀገራቸው ውስጥ በየጊዜው የሚመጡትን አምባገነኖች መታገል አልቻሉም። ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ማኅበረሰብ አለመኖሩን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በኢትዮጵያ ስላለው የፖለቲካ ማኅበረሰብ ከማውራታችን በፊት ስለ ፖለቲካ ባህል በኢትዮጵያ አንዳንድ ነገሮች እንበል።

#### 4.1. የፖለቲካ ባህል በኢትዮጵያ (Political Culture in Ethiopia)

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ባህል በብዙ ችግሮች የተተበተበ ነው። ከላይ ስናያቸው ከነበሩት የተለያዩ ሀገሮች አንጻር ብዙ ሊስተካከል የሚገባ ችግር ይስተዋላል። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ባህል በሁለት መልኩ ከፍሎ ማየት ይቻላል። እነዚህም ሕዝቡ ፖለቲካን የሚረዳበት መንገድ እና ልሂቅ (Elite) የተባለው የህብረተሰብ ክፍል የሚከተለው መንገድ ናቸው።

#### 4.1.1. የኢትዮጵያ ሕዝብ ፖለቲካ አመለካከት

ኢትዮጵያውያን አብረን በጋራ ተደራጅተን መብታችንን ከመጠየቅ ይልቅ መጠራጠር እና በጋራ አለመሥራት የወል ሰብዕናችን ነው። የፖለቲካ ግንዛቤያችን አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የራሳችንን መብት ለመጠየቅ መፍራት ብቻ ሳይሆን ሌላውም ከኛ በአቅም ያነሰ ነው የምንለውን ሰውም መብቱን እንዲጠይቀን፣ አሊያም ተቃውሞውን እንዲተነፍስ አንፈቅድለትም። እንደ ባህል፣ መጠየቅን አናብረታታም። የሚጠይቅ አካልም እንዲሸማቀቅ ይደረጋል።

ይህ አጓጉል ባህላችን በየጊዜው የተለያየ ሀገር አፍራሽ አጀንዳ ይዘው ስልጣን ላይ ለቆዩ እና አሁንም እያስተዳደሩ ላሉ ሀገር ጠል መሪዎች መጠየቅ፣ መሞገት እና መታገል እንዳንችል አድርጎናል። የፖለቲካ ባህላችን ለመጣ ለሄደው አጎብድዶ መገዛት እንጂ ስልጣን የሕዝብ፣ ሀገር የሕዝብ እና ሀብትም የሕዝብ መሆኑን በአግባቡ ባለመረዳታችን ሀገራችንን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ከተናታል። ለጋራ ሀገራችን በጋራ መቆም ሳንችል ቀርተን እንዲያውም በብሄር እና በሀይማኖት ተከፋፍለን ብዙ ጉዳት እያስተናገድን እንገኛልን። ለዚህ ሁሉ ውድቀት የዳረገን የራሳችን የፖለቲካ ባህል እና ደካማ የሆነ የመጠየቅ ባህላችን መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

#### 4.1.2. የልሂቅ (Elite) የፖለቲካ ባህል

የተማረው የህብረተሰብ ክፍል የፖለቲካ እንቅስቃሴው ከሌሎች ሀገራት አንጻር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው። በጣም ውስን ቁጥር ያለው ልሂቅ በተለያየ አደረጃጀት ገብቶ የፖለቲካ ትግል እያደረገ ቢመስልም ዳሩ ግን የሀገርን አንድነት የሚያስጠብቅ ሳይሆን የራሱን የግለሰቡን ጥቅም መሠረት ያደረገ፣ አለፍ ሲልም ብሄር ወይም ሀይማኖት ውስጥ የተወሸቀ ልፍስፍስ ልሂቅ ነው። አብዛኛው ልሂቅ ሥልጣን ከያዘው አካልና ከባለጊዜ ጋር የተቆራረጠ ሳይሆን በተፅዕኖ ስር የወደቀ አለፍ ሲልም ገዥውን አካል መሞገት ለቅስፈት ይዳርጋል በሚል የፍርሃት ቆፈን ውስጥ የተደበቀ ነው። በዚህም ምክንያት ልሂቁ የግለሰብ ፍላጎቱን ሰብሮ፣ የብሄር አጥርን ጥሶ፣ በሀይማኖት መሸበብን አልፎ እና ሌሎች ንዑስ ማንነቶችን አልፎ ለሀገር አንድነት፣ ለሕዝብ ስልጣኔ እና ለዘላቂ ሰላም አማራጭ ሀሳብ የማያመጣ፣ የማይታገል እና በአጠቃላይ የፖለቲካ ማኅበረሰብ የሚለውን መገለጫ የማያሟላ ነው።

ድል ለአማራ ሕዝብ!

ሰላም ለኢትዮጵያ!

ረቡዕ ጳጉሜ ፭ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.
ኢትዮጵያ።

በክፍል 2፤ "አማራ እንደ ፖለቲካ ማኅበረሰብ ሲገመገም" ይቀጥላል። በቀጣይ እትም ይጠብቁን።

## Political Community and Liberation Struggle!

(Contiued from page 1)

Thomas Hobbes, in his book *Leviathan*, has explained at length the role that an organized population can play. Hobbes argues that a political community can save a nation from chaos and barbaric impulses, serves as the foundation for a beneficial state institution in the political sphere, is the only solution to prevent anarchy and descent into turmoil. The common point of the ideas mentioned above is that an organized and politically mature population can create a system capable of bringing stable and lasting peace.

### 3. Organizations That Created Strong Political Communities and Their Outcomes

Strong organizations perform various tasks to elevate their countries to a better level. One of the most important among these is educating and organizing the population to unite for their country. This task of uniting the population is extremely challenging, demanding numerous efforts, vision, and long-term thinking. Organizations that have practically achieved this have placed their countries in a great position. The liberation journeys of Vietnam and China, cited below, are enduring examples that have inspired and guided many countries. Although the specific national liberation conditions of those countries may not directly apply to our country, the method of creating a political community is always worth learning from at any time or place.

#### 3.1. Ho Chi Minh and the Communist Party of Vietnam

Among the countries that waged liberation struggles in the 20th century in our world, Vietnam stands out as the earliest example. Vietnam, divided into two parts by the Cold War North and South with the North socialist and the South capitalist puppet, initially endured under French rule and later American support until the Geneva Accords. Realizing that Vietnam's unity was at risk, the country's visionary leaders awakened the Vietnamese people to fight for their independence and unity. Among these, Ho Chi Minh was the main one. Ho Chi Minh,

traveling between China and Vietnam from 1924-1930, made great efforts to establish a Marxist-Leninist party capable of providing early leadership to this complex struggle. Initially, he mobilized the "youth" through the newspaper called the "Youth" to engage the youth in the struggle. After much effort and struggle, in 1930, he founded the Indochinese Communist Party (later the Vietnam Independence Party, today the Communist Party of Vietnam).

In 1935, at the Communist International Congress in Moscow, based on the decision to establish a broad anti-imperialist democratic front, Ho Chi Minh, using the name Nguyen Ai Quoc, established a broad anti-imperialist front, enabling the entire population to participate in the struggle. In the historic Dien Bien Phu campaign, by defeating the French forces, France was forced to recognize Vietnam's unity through the Geneva Accords. However, starting from 1955, American imperialism, replacing French influence, launched a war by building military bases and using internal traitors to subdue the southern region. The Vietnamese people, loved by global peace advocates, confronted American imperialism head-on with determination. Despite the American army having over half a million soldiers and spending billions of dollars, it could not defeat the Vietnamese people. The one who led this effort was the Communist Party of Vietnam. Ho Chi Minh, the ideological leader of this party, spent his entire life in the struggle and became a great leader closely tied to Vietnam's liberation history. Ho Chi Minh created a political community by educating and empowering the population with a collective vision.

**3.2. Mao Zedong and the Chinese Communist Party**

Among the countries in our world that suffered from extreme poverty and problems, China is one. Mao appropriately identified China's problem as the overwhelming backwardness of the Chinese people after feudalism, and he concluded that relying on the peasants as the foundation to mobilize and later liberate the population from backwardness would not yield results, nor would urban-based struggles. Hence, he decided that the war must be based on mass mobilization: based on this principle, he mobilized various classes among the peasants to participate in the struggle. Among these, he established peasant associations, peace and security forces, and bureaucrat capitalists, along with other positions. By doing this, he created conditions for the rural population to participate as owners in the revolutionary struggle, allowing their political maturity to grow.

Recent studies show that organizations conducting liberation struggles, during the struggle, established higher administrations in controlled areas and conducted only narrow studies focused solely on warfare; those that only conducted warfare after gaining power as the basis failed in the process or did not bring change, as confirmed. Mao's liberation strategy, by establishing a higher administration, provided long-term practice, making its end result very effective. The reason for this success was creating a cohesive political community through their ideology and practical actions.

Mao made his program accessible to the people by placing it in his book *Quotations from Chairman Mao Tse-tung* (Red Book) to make the people's commitment to the struggle fervent. Millions of Chinese memorized the Little Red Book exactly like a religion and accepted it. The Quotations, second only to the Bible in global sales, has been printed 900 million times to date. When discussing Chinese unity, although China has ethnic, religious, and other identity differences, under leaders like Mao, the difficult period was bridged with a unity promoter they lacked. To understand today's Chinese advancement, it is essential to recognize the existence of this political community.

**4. Political Community in Ethiopia**

Ethiopia is a country that has made significant contributions to Africa's political history. Ethiopians, having defended their country from external enemies, have served as examples of the path to freedom for other black peoples. However, while they have collectively protected their country from external threats, they have not been able to liberate themselves from the anarchies that arise internally from time to time. This reveals the absence of a political community in Ethiopia. Before examining the political community in Ethiopia, let us look at some aspects of the political culture in Ethiopia.

**4.1. Political Culture in Ethiopia**

The political culture in Ethiopia is fraught with many problems. Compared to the various countries mentioned above, it seems full of problems that need to be addressed. The political culture in Ethiopia can be viewed in two ways: how the people perceive politics and the way the elite group called the "literate" operates.

**4.1.1. The Ethiopian People's Attitude toward Politics**

We Ethiopians, instead of collectively organizing and demanding our rights, have a culture of individual begging and not working together. Our political participation stems not only from demanding our own rights but also from enabling the weaker one among us to claim their rights and encouraging resistance. As a culture, demanding is considered noble: it even allows the demanding entity to be heard.

This subservient culture of ours has enabled the dictators who ruled and still rule our country at various times to demand, beg, and liberate us. Because we do not understand that political culture should serve the people, and that power, the country, and wealth belong to the people, our country has fallen into great trouble. Unable to stand together for our collective country, we have suffered much damage by dividing ourselves by ethnicity and religion. For all this loss, it seems appropriate to blame our own political culture and the weak culture of demanding.

**4.1.2. Elite Political Culture**

The political actions of the educated segment of society appear extremely selfish compared to other countries. Although a small number of elites seem to engage in political struggle at various levels, in reality, instead of preserving national unity, they act based on personal gain, and when they fall, they become fragmented elites divided by ethnicity or religion. The majority of the elite, instead of being restrained by the power they hold and time, fall into the cycle of corruption by coveting the official's wealth. For this reason, the elite secretly prioritize personal interests, incite ethnic strife, ignore religion and other identities, and do not produce ideas for national unity, popular sovereignty, and lasting peace; they do not empower and, in general, do not fulfill the purpose of what is called a political community.

**In part 2, "Considering Amhara as a Political Community" will continue in the next issue.**

Victory to the Amhara People!
Peace for Ethiopia!
September 10, 2025.
Ethiopia.

## ከድሮን ጥቃት ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ መርሆች

(ከገጽ 1 የቀጠለ)

በተለይም የክረምቱ ወራት መገባደዱን ተከትሎ የበቃው ወቅት ድሮን ለመጠቀም ምቹ ያደርገዋል። አገዛዙ በሁሉም ግንባሮች እየተመታ የእግረኛ ሰራዊቱ እየተመናመነ እና የውጊያ ስነ-ልቦናው እየተቀዛቀዘ መምጣቱን በመገምገም በድሮንና አየር ኃይል የታገዘ ውጊያ ለመክፈት እንዳቀደ መረጃዎች እየወጡ ይገኛሉ። የተለያዩ የድሮን ምርቶችንም በገፍ ከማስገባት ጀምሮ ከሰሞኑ መደበኛ የድሮን ቅኝት በሁሉም አካባቢዎች እያደረገ መሆኑም ተረጋግጧል። በመሆኑ ሁሉም የፋኖ አደረጃጀት የጥንቃቄ መርሆችን ከመተግበርም በላይ የውጊያ ስልቱን ማዘመን ይገባዋል።

**የድሮን ጥቃቶች ዋና ኢላማ የሚያደርጉት ምን ላይ ነው?**

- ✓ የስብሰባ ቦታ፣
- ✓ የአመራር መቀመጫ፣
- ✓ የመኪና ትራንስፖርት፣
- ✓ የስልጠና ቦታ፣
- ✓ የሰራዊት ካምፕ ወዘተ የትኩረት ነጥቦች ናቸው።

# የአማራ ፋኖ ድምፅ

Vol. 1; No. 4
አንደኛ ዓመት አራተኛ እትም

## ከድሮን ጥቃት ለመከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ ምክረ-ሃሳቦች

ተገቢ ጥንቃቄ በማድረግ የድሮን ጥቃትን መከላከል ይቻላል። በየአደረጃጀታችን የሚመለከተው ክፍል የሚሰጠው ስልጠና እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን የጥንቃቄ ስልቶች ተግባራዊ እንድናደረግ ለመጠቆም እንወዳለን።

1. በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው አካላት ለሁሉም አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫና የጥንቃቄ ፕሮቶኮል ደንብ ማዘጋጀትና መተግበር ያስፈልጋል፣
2. የትኛውም የታጋይ አባላትና አመራር ስብስብ በተለይ ስልጠና፣ ምግብና፣ ውይይት፣ ትራንስፖርት ወዘተ በመረጃና ደህንነቱ የተጠና እና የተፈቀደ ሊሆን ይገባዋል፣
3. ለድሮን ካሜራ በቀላሉ እይታ ውስጥ የሚገቡ ሁኔታዎችን በአሰራር ደረጃ ማስተካከል (አብለጭላጭ ነገሮች፣ የተለዬ አለባበስ፣ ከከለላ ውጭ ያሉ ስብስቦች፣ ጂፒኤስ ያላቸው ስልኮች፣ ተጋላጭ የሆኑ ካምፖች፣ ወዘተ) ጥንቃቄ የሚሹ ይሆናል፣
4. የድሮን ቅኝት መኖሩ ሲታወቅ ወይንም ድምጽ ሲሰሙ ስብስብን መበተንና ከለላ ያለው ቦታ በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል፣
5. ድሮን ከጣለ በኋላ በአየር ላይ እንዳለ ድጋሚ የሚጥልበት እድል ሰፊ ስለሆነ በተለይም ቁስለኞችን ለማንሳት ወይን በድንጋጤ ፈጥኖ መሰባሰብ ለተጨማሪ ጥቃት ሊያጋልጥ ስለሚችል ጥንቃቄ ያስፈልጋል፣
6. ካምፕ አካባቢ ወይንም የምሽት ስብሰባ ላይ መብራትን ማጥፋት ያስፈልጋል፣
7. በምንም አይነት መንገድ ሰራዊት ጭኖ በመኪና መንቀሳቀስ በእጅጉ አደገኛ ስለሆነ በእግር ብቻ መጓዝ መለመድ አለበት፣
8. የሰራዊት እንቅስቃሴ ሲደረግ ተገቢ ርቀትን (25 ሜትር ርቀት) ጠብቆ መጓዝ የስፈልጋል፣
9. የስብሰባ ፕሮግራሞችን የተሳታፊ ቁጥር በመቀነስ እንዲሁም ጥቅጥቅ ያሉ ጫካዎችን በመጠቀም ከካሜራ እይታ ውጭ ማድረግ፣
10. አንድ ቦታ ላይ ረጅም ስዓት አለመቆየት፣ ቦታውን ለጥቆማ እንዳይመች ማድረግና ያሉበትን ቦታ በየስዓቱ መቀያየር፣
11. እንቅስቃሴዎች ሲኖሩ የደመና መጠን ከፍተኛ በሚሆንበት ወይንም ምሽት አካባቢን መጠቀም የተሻለ ያደርገዋል። ሆኖም አንዳንድ ሰው አልባ ድሮኖች ሙቀት በመሰብሰብ ወደ ምስል ቀይረው መረጃ የሚሰጡ ድሮኖች መኖራቸውን ያስታውሱ፣ ስለዚህ በምሽት የሚደረግ እንቅስቃሴ ምንጊዜም ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባል፣
12. ድሮን ቅኝት እያደረገ ከሆነ ወይንም በአካባቢው መኖሩ ከታወቀ በዝግታ እና በተረጋጋ ሁኔታ በመንቀሳቀስ (ሩጫ ትኩረትን ሊስብ ስለሚችል) የተሻለ ቦታ መያዝ የስፈልጋል፣
13. አንድን መንገድ በተደጋጋሚ አይጠቀሙ፤ የሚጓዙባቸው መንገዶች ደጋግመው የሚሄዱባቸው ከሆኑ ለድሮን ኦፕሬተሮች ያሉበትን አካባቢ እንዲያውቁ እድል ይከፍትላቸዋል፣
14. ከመልከዓ-ምድር ጋር ሊመሳሰል የሚችል መሸፈኛ ይጠቀሙ፡- እንቅስቃሴዎትን ለመደበቅ ተፈጥሯዊ ከሆነ ወይም ሰው ሰራሽ ከሆነ መሬት ወይም መልከዓ-ምድር ገጽታ ሊመሳሰሉ የሚችሉ መሸፈኛዎችን ይጠቀሙ። ይህም በሸለቆዎች፣ ጥቅጥቅ ባሉ ደኖች ወይም በከተማ አካባቢዎች ላይ ሲንቀሳቀሱ በከፍታ ላይ ከሚበሩ ድሮኖች እዕታ ውጪ እንዲሆኑ ይረዳዎታል፣
15. ምንም አይነት ዱካ አለመተው:: ሰው አልባው ድሮን የእርስዎን ዱካ ለመከተል እና ፍንጭ ለመስጠት የሚያስችለውን ለምሳሌ እንደ ተሽካርካሪ ያሉ ዱካ፤ በጉዞ ላይ እያሉ የረገጧቸው የተለያዩ እጽዕዋቶች እና መሰል አሻራዎች ምልክት ሊሰጡ ስለሚችሉ አሻራን እያጠፉ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው።
16. ፀረ- ድሮን መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ ማዋል፣
17. የመረጃ መለዋወጫ ማዕከል (information center) በየአደረጃጀቱ ማዋቅርና ወቅታዊ የመረጃን ማግኘት፣ መናበብ፣ እርስ በርስ መተባበር፤ አንዱ ያላወቀውን ላንዱ ማስረዳት እና ግንዛቤ ማስጨበጥ በተለይም የድሮን ቅኝት መኖሩ ሲታወቅ ስልክ ደውሎ ለሁሉም መረጃና ደህንነት አባላት ማሳወቅና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፣

## A New Year's Message from Amhara Fano People's Organization (AFPO) (continued from Page 1)

This new year is not just a change in the calendar—it is a call to unity, discipline, and purpose. The Amhara struggle has reached a decisive moment, and AFPO stands ready to work with clarity, structure, and unwavering commitment to unity among all Fano factions.
Our Chairman, Fano Eskinder Nega, recently declared:
"We are not here to compete with our fellow Fano brothers—we are here to unite with them. The survival of our people demands it. The time for fragmentation is over; the time for unity is now."
This message is not isolated. It is echoed by all AFPO leadership, both in public and private forums. As stated in our New Year covenant:
"Fano unity is not a slogan—it is a moral obligation. To dismantle the oppressive regime and liberate the people, standing together as one is a sacred duty."
Recently, on New Year's Eve, the top leadership of AFPO reaffirmed our unwavering commitment to unity in an interview with Anchor Media. This public declaration once again made it clear:
"Unity of FANO is our central and core value."
AFPO is not just another faction—it is the only stable, structured, and transparent organization within the Fano movement. We have endured trials, navigated internal challenges with maturity, and emerged stronger. Our leadership is defined by discipline, democratic values, and a long-term vision for justice and national renewal.
In this spirit of unity, AFPO also calls upon the global Amhara diaspora—activists, professionals, youth, and elders—to stand as one with the resistance at home. The diaspora has been a vital force in advocacy, fundraising, and international engagement.
We also urge all Fano groups and leaders to approach the unity process with genuine intent, humility, and strategic patience. The path to unity can be fragile, and careless actions or performative gestures can create unnecessary obstacles. This is a time to listen more, coordinate better, and act with the seriousness the moment demands. Our people's survival and final victory depend on it.
AFPO's diplomatic engagements with global actors have exposed the deceptive narratives of the Prosperity Party (PP) regime, and have elevated the Amhara cause to a new level of international legitimacy and moral clarity.
If we unite, our voices can be heard even much louder and clearer—across Ethiopia and around the world.
Let 2018 E.C. be remembered as the year we turned the page on division and wrote a new chapter of solidarity, strength, and victory.

AFPO – Standing Strong, Leading Forward.
Happy New Year!

## መልካም አዲስ ዓመት፣ ፳፻፲፰፣ ከአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አፋሕድ) (ከገጽ 1 የቀጠለ።)

የአፋሕድ ሊቀመንበር ፋኖ እስክንድር ነጋ በቅርቡ አንዳሉት፤ "እኛ የወጣነው ከፋኖ ወንድሞቻችን ጋር ለመታገል አይደለም - የወጣነው ከነሱ ጋር አንድነት ለመፍጠር ነው፤ የሕዝባችን ህልውና የሚጠይቀው እሱን ነውና። የመበታተን ጊዜ አልፏል፤ የአንድነት ጊዜው አሁን ነው።"

ይህ መልእክት የተነጠለ አይደለም። በሕዝብም ሆነ በግል መድረኮች በሁሉም በተገኙ አጋጣሚዎች ላይ በአፋሕድ አመራሮች ተስተጋብቷል። በአዲስ ዓመት ቃል ኪዳናችንም ላይ እንደተገለጸው፡- የፋኖ አንድነት መፈክር አይደለም - የሞራል ግዴታ ነው። ጨቋኙን ሥርዓት አፍርሶ ህዝብን ነፃ ለማውጣት አንድ ላይ መቆም የተቀደሰ ተግባር ነው።

በቅርቡ፣ በአዲስ ዓመት ዋዜማ፣ የአፋሕድ ከፍተኛ አመራሮች ከአንከር ሚዲያ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለአንድነት ያለንን የማያወላውል ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል። በዚህ የሚዲያ ማብራሪያ በድጋሚ ለማረጋገጥ እንደተሞከረው፤ የፋኖ አንድነት ማዕከላዊ እና ዋና እሴታችን ነው።


አፋሕድ አደረጃጀት ብቻ አይደለም - በፋኖ እንቅስቃሴ ውስጥ ብቸኛው የተረጋጋ፣ የተዋቀረ እና ግልጽነት ያለው ድርጅት ነው። ችግሮችን ተቋቁመናል፣ ውስጣዊ ፈተናዎችን በብስለት ተራምደን ይበልጥ ተጠናክረን ወጥተናል። አመራራችን ፍትሕንና የሀገርን ተሃድሶ ለማንበር በዲሲፕሊን፣ በዲሞክራሲያዊ እሴቶች እና በአርቆ አሳቢነቱ ይገለጻል።

በዚህ የአንድነት መንፈስ፣ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የአማራ ዲያስፖራዎች - አንቂዎች፣ ባለሙያዎች፣ ወጣቶች እና አረጋውያን - በሀገር ውስጥ ካሉት ታጋዮች ጋር አንድ ሆነው እንዲቆሙም አፋሕድ ጥሪውን ያቀርባል። ዳያስፖራው በማስተባበርና፣ ገንዘብ በማሰባሰብ እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ተሳትፎ ወሳኝ ሃይል ነው።

እንዲሁም ሁሉም የፋኖ ቡድኖች እና አመራሮች ወደ አንድነት ሂደቱ በቅን ልቦና በሀቀኝነትና በዘላቂ ግብ ላይ ተመስርተው ሊቀርቡ ይገባል። ወደ አንድነት የሚወስደው መንገድ በጥቃቅን ጉዳይ እንቅፋት ሊገጥመው ከቻለ ሂደቱም ውጤቱም ሊጎዳ ይችላልና በከፍተኛ ጥንቃቄ ልንይዘው ይገባል።

ይህ ጊዜ የበለጠ ለማዳመጥ፣ በተሻለ ሁኔታ ትብብር ለመፍጠር እና የጉዳዩ አሳሳቢነት በሚጠይቀው ልክ የምንወስንበት ጊዜ ነው። የህዝባችን ህልውና እና የመጨረሻው ድል በዚህ አቋማችን ላይ የተመሰረተ ነው። የአፋሕድ ከአለምአቀፍ ተዋናዮች ጋር ያደረገው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የብልጽግና ፓርቲ (PP) አገዛዝን አታላይ ትረካዎች በማጋለጥ የአማራን ጉዳይ ወደ አለም አቀፍ ህጋዊነት እና የሞራል ግልጽነት ደረጃ ከፍ አድርጎታል። ከተባበርን ድምጻችን ከፍ ያለ እና ግልጽ በሆነ መልኩ ይሰማል - በመላው ኢትዮጵያ እና በመላው አለም። 2018 E.C የልዩነትን ምዕራፍ ዘግተን አዲስ የአብሮነት፣ የጥንካሬ እና የድል ምዕራፍ የምንጽፍበት ዓመት ይሆናል።

አፋሕድ - በጠንካራ አቋም አሁንም ወደፊት ይገሰግሳል!



# በምስሎች In Pictures

